Governmental and non-governmental organizations such as Sitti Heritage Foundation have taken a number of measures for the enactment and transmission of the element.

### 5.3 Threats to the Enactment:

#### 5.3.1 Physical Threats

There are no physical or material threats associated with the practice of the heritage. When crimes occur among the Somali-Issa community, Guddi assembly judges gather under the shade of trees used as courts by the community to resolve conflicts between individuals or groups. The punishment levels set by the law will be applied according to the severity of the crime. Often, minor cases are heard and resolved. For serious crimes, such as murder, blood indemnity is enforced in the middle of a river.

The traditional laws played an important role to reconcile those who have been quarreled in the Somali-Issa communities and return to their previous peaceful life. There are no physical or material threats to be mentioned as such.

#### 5.3.2 Socio-Economic Threats

The oral customary laws are being implemented in harmony with the formal law. From an economic point of view, it does not cause the society to various abuses and expenses. The service works in a way that saves energy, time and cost for the community members. At the same time, since the wrongdoer and the victim will be judged according to the law, there are no winners and losers.

However, modernization has become one of the challenges that hinder the traditional laws from being properly implemented. For example, the community members, especially the youth, that emigrate from the countryside to the city and getting accustomed to modern life pay little attention to the oral customary laws and are leaning towards official courts instead.

In addition to this, some of the Guddi and Gande fathers and elders of the Somali-Issa communities, who know the culture and the traditional law well, are passing away before transmitting the knowledge and skills to the young generation as expected.

However, Somali Region Culture and Tourism Bureau, non-governmental organizations such as Sitti Heritage Foundation and the community at all levels and individuals are working closely together to address the problem presented as threats by using formal and informal channels of communication and audio visual records and documentations to transmit the knowledge associated with the oral customary laws.

The values and importance of this intangible heritage has been promoted through panel discussions, symposiums and through the use of print and electronic media.

### 5.4 Safeguarding Measures in Place

The Ethiopian Somali Regional State and other governmental and non-governmental organizations such as Sitti Heritage Foundation have taken a number of measures to safeguard this intangible heritage. They allocate budget to undertake various safeguarding activities with the participation of the concerned community members. Various research works have been conducted on Xeer Ciise. The bearers and practitioners are also involved in the joint research projects undertaken so far.

Promotion of Xeer Isee and raising its awareness is undertaken through brochures and the various media such as radio and television programs in Somali Language. The oral customary laws are promoted as the shared heritage beyond the borders by organizing events, symposiums, seminars and meetings with joint participation of bearers and practitioners of the element from the three countries..

Efforts are being taken to preserve the cultural places such as Sitti Mountain, the twelve rivers and tree shade areas associated with Xeer Ciise. The necessary infrastructure will be built for these cultural places in the future to facilitate tourism.

The Ethiopian Heritage Authority in collaboration with Ethiopian Somali Regional State Culture and Tourism Bureau, Sitti Heritage Foundation, Djibouti National Agency to promote Culture and Somalia have nominated the Oral Customary Laws of Somali-Issa Communities for inscription on the Representative List of Intangible Cultural Heritage of Humanity by UNESCO.

## 6. Data Gathering and Inventorying

### 6.1 Consent from and Involvement of the Community/Group in Data Gathering and Inventorying

The Ethiopian Heritage Authority (EHA) as well as the Culture and Tourism Bureau of Somali Region and Sitti Heritage Foundation have participated in the national inventory of Xeer Ciise. After making preliminary preparation and reviewing, experts of Ethiopian Heritage Authority and Sitti Heritage Foundation directly proceeded to the inventorying process. Representatives of the Somali-Issa communities have participated and contributed their share towards the success of this inventory.

Moreover, the Ugaz (political leader and spiritual father of the Somali-Issa), prominent individuals, scholars, assemblies of judges and heads of government bodies have freely participated in the course of interviews and focus group discussions held in the process of data gathering. Relevant governmental and non-governmental institutions have also provided their comments on the inventory with due responsibility and commitment.

### 6.2 Restrictions, if any, on Use of the Inventoried Data

There is no restriction or limit to the use in utilization of the data as resource towards the effort in promoting and developing this intangible heritage and raising awareness about its importance. However, unauthorized utilization of the data without consent from the legal authorized entity as well as the custodians is not permitted. Moreover, using the heritage for activities of personal gains, for commercial purposes and other activities basing private interest or acts that are contradicting the custom shall be subject to legal accountability in accordance with the relevant laws of the country.

### 6.3 Date and Place of Data Gathering

The element was inscribed in the National Register of the Intangible Cultural Heritage of Ethiopia under register No. 0008 on November 4, 2022 (ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ.ም ). Data for this inventory has been collected from Ethiopian Somali Regional State, Jigjiga, Aysha, Dire Dawa, Djibouti and Somalia.

### 6.4 Responsible Body to the National Inventory/Register of the element

The national register of the Xeer Ciise is undertaken by the experts of Heritage Research and Study Directorate of the Ethiopian Heritage Authority (Gezahegne Girma and Kelemuwa Mekonen in co-operation with Somali Regional State Culture, Heritage and Tourism Bureau, Sitti Heritage Foundation Head Woizero Ayan Ali, Ato Abdurahman Usman and Dr. Ali Abdulahi. The authority section in charge of the approval of the inventory is the Heritage Inventory, Inspection and Standardization Directorate of the Ethiopian Heritage Authority.

Andualem Girmaye

Cultural Heritage Research Directorate Director

Federal Democratic Republic of Ethiopia * Ministry of Tourism * Ethiopia Heritage Conservation Authority

17 MAR. 2023

የማይዳሰስ (ኢንታንጀብል) ባህላዊ ቅርስ በአገር አቀፍ ደረጃ ለመመዝገብ የተዘጋጀ የኢንቬንቶሪ ፎርማት

Format for national register of the intangible cultural heritage of Ethiopia

መለያ ቁጥር 0008

Register no. 0008

1. ዳራ (background)

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት ከተዋቀሩ አሥራ አንድ ክልሎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ብሔረሰቡ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሱ የሆነ ታሪክና ባህል ያለው ሕዝብ ነው፡፡ የሶማሌ ኢሳ ማኅበረሰብ ባህላዊ ሕግ ወይንም በብሔረሰቡ አጠራር ሔር ኢሴ (Xeer Ciise) አንዱ የማኅበረሰቡ መገለጫ እሴት ነው፡፡

ከሶማሌ ብሔረሰብ መካከል ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢሳ ማኅበረሰብ ዓባላት በድሬዳዋ ከተማና በሲቲ ዞን ይኖራሉ፡፡የሲቲ ዞን በሶማሌ ክልል ከተዋቀሩ አሥራ አንድ ዞኖች መካከል አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያን ከጅቡቲና ሶማሊያ ጋር የሚያዋስን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የኢሳ ማኅበረሰብ በጅቡቲ ከአፋሮች ጋር በጋራ የሚኖር ሲሆን በሶማሌ ላንድ ደግሞ ግማሽ ያህሉ የኢሳ ማኅበረሰብ እንደሆነ ይገለጻል፡፡

በአጠቃላይ የኢሳ ማኅበረሰብ በምሰራቅ አፍሪካ በተለይም በአፍሪካ ቀንድ አገራት ላይ በብዛት የሚኖር ሕዝብ ነው፡፡ የሕዝቡ የኢኮኖሚ መሠረት በከተማ ያለው በንግድ የሚተዳደር ሲሆን በገጠር ያለው ደግሞ በአርብቶ አደርነት የተሠማራ ነው፡፡ በእነዚህ ሦስት የተለያዩ አገራት የሚኖሩ የማኅበረሰቡ ክፍሎች አንድ የሚያደርጋቸውና የሚያስተሳስራቸው የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው አንድ የጋራ መተዳደሪያ ባህላዊ ህግ ወይንም በማኅበረሰቡ አጠራር ‹‹ Xeer Ciise ሔር ኢሴ›› ያላቸው መሆኑና በዚሁ ባህላዊ ህግ በፍትህና በእኩልነት የሚተዳደሩበት መሆኑ ነው፡፡ ሌላውና ዋነኛው ጉዳይ ደግሞ በሦስቱም አገራት የሚኖሩ የማኅበረሰቡ አባላት የአስተዳደር ማዕከሉን ወይንም መቀመጫውን በኢትዮጵያ ድሬዳዋ ከተማ ባደረገ አንድ መሪ ወይንም በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ኡጋስ›› መመራታቸው ነው፡፡

ባህላዊ ህጉ ከዛሬ አምስት መቶ ዓመታት በፊት የተዘጋጀና አገልግሎት እየሰጠ ያለ ሲሆን ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ እስከአሁን ድረስ እየተተገበረ ያለ የማኅበረሰቡ ህያው የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ነው፡፡ ይህ ባህላዊ ህግ በሦስቱም አገራት በሚኖሩ የማኅበረሰቡ አባላት ዘንድ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው፣እኩል የሚተዳደሩበትና የሚጠብቁት እንዲሁም ለቀጠናውየሰላም መሠረት የሆነ የጋራ ሀብት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህ አገር አቀፍ ኢንቬንቶሪም የማኅበረሰቡ ህያው ሀብትና የመተዳደሪያ ህግ በሆነው የማኅበረሰቡ ባህላዊ ህግ ወይንም በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ሔር ኢሴ››ን የተመለከተ ነው፡፡

2. የማይዳሰስ ቅርሱ መረጃ

2.1 የቅርሱ ምድብ (Domain)

የኢሳ ማኅበረሰብ ባህላዊ ህግ አፋዊ (ቃላዊ) ትውፊቶችናመገለጫዎች፡-(oral traditions and expressions, including language as a vehicle of the intangible cultural heritage)፣ማኅበራዊ ክንዋኔዎችና ሥነ-ሥርዓቶች (Social practicesand rituals)፣ ስለ ተፈጥሮና ዓለም ዕውቀትናትግበራ ወይም አገርበቀልዕውቀቶች (knowledge and practices concerning nature and the universe)፣ ትውፊታዊ የዕደ ጥበብ ዕውቀቶችና ክህሎቶች (traditional crafsmanship) እና ትውን ጥበባት (performing arts)ውስጥ ሊካተት ይችላል፡፡

2.2 የቅርሱመጠሪያ በማኅበረሰቡ/በቡድኑ ቋንቋ (Name of the element, as used by community or group concerned)

ሔር ኢሴ (Xeer Ciise) ነው፡፡

2.3 የቅርሱ ባለቤት ማኅበረሰብ፣ ቡድን ወይም ግለሰብ ( Community(ies), group(s) or individuals concerned )

የቅርሱ ባለቤት በኢትዮጵያ፣ በጅቡቲ እና በሶማሌ የሚኖሩ የሶማሌ ኢሳ ማኅበረሰብ አባላት ናቸው፡፡

2.4 ስለ ቅርሱ ምንነት ማብራሪያ (Description of the element)

የኢሳ ማኅበረሰብ ባህላዊ ህግ የማኅበረሰቡ የማንነት መገለጫና ለረጅም ዘመናት ሲተገበረው የኖረው የዘላቂ ሰላሙ ማስጠበቂያናባህላዊ እሴቱ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ በሦስቱም አገራት የሚኖሩ አባላቱን እንደየሚኖሩበት አገር ነባራዊ ሁኔታ በእኩልነትና በፍትኃዊነት ከሚያስተዳድርበት ባህላዊ ህግ ባሻገር ሌሎች በርካታ መገለጫ የሆኑ የማይዳሰሱ ቅርሶችና እሴቶች ያሉት ሕዝብ ነው፡፡ ከእነዚህ እሴቶቹ መካከል ሀገረሰባዊ ጭፈራዎች፣አፋዊ ትውፊቶች፣ የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት፣ ልዩ ልዩ ባህላዊ ጨዋታዎች፣ ባህላዊ አልባሳትና አለባበሶች፣ ባህላዊ አጊያጌጦች፣ ባህላዊ ምግቦችና የአመጋገብ ሥርዓቶች፣ ሀገረሰባዊ የዕደጥበብ ዕውቀቶችና ክህሎቶች የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በአንድነት ተከባብሮ የመኖር በጥቅሉ የአብሮነት ህይወት ተምሳሌትነታቸው የሆኑ ለዘመናት በትውልዶች ቅብብል የደረጁ ባህላዊ እሴቶች አማካይነት ጠንካራ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርና ግንኙነት ያላቸው መሆኑ ከሚጠቀሱ ጥቂት መገለጫዎቻቸው መካከል ናቸው፡፡

የኢሳ ሶማሌ ማኅበረሰብ ባህላዊ ህግ ወይንም ሔር ኢሴ ታሪካዊ ዳራ ወይንም አመሠራረት የሚጀምረው ከአምስት መቶ ዓመታት በፊትበ16ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ አባቶች ይህን ሕግ ለማርቀቅና ለማሻሻል የተለያዩ ቦታዎች የተቀመጡ ሲሆን በመጨረሻ ላይ ግን «ሲቲ ተራራ» ላይበመቀመጥ የአሁኑን «ሔር ኢሴ» የተባለውን ህግ እንዳረቀቁት ይገለጻል፡፡ ህጉን በጊዜው ያረቀቁት አባቶች 44 ሲሆኑ 44ቱም ከኢሳ ብሄረሰብ ተወክለው የተውጣጡ ናቸው፡፡ እነዚህ አካላት በህጉ መሠረት ገንዴ ይባላሉ፡፡ ይህ ባህላዊ ህግ በሂደት ብዙ ማሻሻያዎችከተደረጉበት በኋላ ወደ ሙሉ ትግበራ እንደገባ ተያይዞ ይገለጻል፡፡ ህጉን ለማሻሻል በጊዜው የነበሩትን የጎሳው አባቶች፣ የማኅበረሰቡ ምሁራንና አዋቂዎች ሰብስቦ ሥራውን እውን ለማድረግ ዓመታት እንደፈጀባቸው ይነገራል፡፡በዚህም ሁኔታ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮየኢሣ ሶማሌ ማኅበረሰብ አባላት በዲሞክራሲያዊ መንገድ በራሳቸው በተረቀቀ ባህላዊ ሕግ መሠረትይተዳደሩ እንደነበር ይነገራል፡፡

ሕጉ የተረቀቀበት ሲቲ ተራራ በሶማሌ ክልል ሲቲ ዞን አይሻ ወረዳ በላስ ሀዳድ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ የተራራው አቀማመጥ ሁለት የተገጣጠመ ሲሆን አንደኛው ህግ አውጪ አባቶች ሲቀመጡበት ሌላኛውን ደግሞ እነሱን የሚጠብቁ ወታደሮች ይቀመጡበት ነበር፡፡ በዚህ ተራራ ላይ እስካሁን ድረስ በዚያን ጊዜ ባህላዊ ሕጉን ያረቀቁአባቶች ይቀመጡበት የነበሩ ድንጋዮች ይገኙበታል፡፡ በሕጉ ማርቀቅ ሂደት የተሳተፉ አባቶችየየራሳቸው ንዑስየጎሳ ክፍል ምልክት በእነዚህ በተራራው አናት ላይ ባሉ ጠፍጣፋና ለመቀመጥ ምቹ የሆኑድንጋዮች ላይ አኑረውባቸዋል፡፡ አባቶች በዚያን ጊዜ ጦርነት ይበዛባቸው ስለነበር ሥፍራው ጠላት እየመጣባቸው እንደሆነና እንዳልሆነ ለመለየት በአራቱም አቅጣጫ ረጅም ርቀት የሚያሳያቸው በመሆኑ ጭምር የተመረጠ እንደሆነ ይነገራል፡፡

ኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ እ.ኤ.አ. ሰሜን ኢትዮጵያን በጦርነት ካዳረሰና ገዥነቱንና የበላይነቱን ካረጋገጠ በኋላ እ.ኤ.አ. ከ1535 እስከ 1543 ድረስ በደቡብ ጎንደር ደምቢያን የፖለቲካ እና የእስልምና ሃይማኖት ማዕከል በማድረግ የሰሜንና የምስራቅ ሕዝቦችን እንዲሁም የሶማሌ ሕዝቦችን ጨምሮ ሲያስተዳድር መቆየቱ ይታወሳል (Trimingham፣ 1965፣87)፡፡ ይሁንና ከፖርቹጋል መንግስት በተገኘ ወታደራዊ እርዳታ ኢማሙ በጦርነቱ ከመቁሰሉም በላይ በፖርቹጋል መድፍና ጠመንጃ ምክንያት የኃይል ሚዛን በመቀየሩ ሊሸነፍ ችሏል (ላጲሶ፣1982፣144) ፡፡

የኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ (አህመድ ግራኝ)ኢስላሚክ ሱልጣኔት በፖርቱጋሎች ከተሸነፈ በኋላ በሰይላ (ዘይላ) አካባቢና በአጠቃላይ በምስራቁ ክፍል ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች በፖርቱጋሎች ብዙ ጫናዎች ይደርስባቸው የነበረ መሆኑ ለአብነትም የንግድ ማዕከላቸው የነበረችው ሲቅጦራ የተባለች ወደብ በፖርቱጋሎች መያዝና በዚህም ምክንያት የውጭ ንግዳቸው በመቋረጡ በአከባቢው ይኖሩ የነበሩት የኢሳ ህዝብ ከተማውን ጥለው ወደ ገጠር በመሄድ እርስ በርስ በሚፈጠሩ ግጭቶችን፣በደሎችንና ከቀላል እስከ ከባድ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከል በቀዳሚነት ሁሉንም እኩል የሚያስተዳድር ህግ መደንገግ አስፈላጊነቱ በማኅበረሰቡ አባላት በመታመኑና ስምምነት ላይ በመደረሱ የኢሣ ሶማሌ ማኅበረሰብ ባህላዊ ህግን ለማውጣት ምክንያት እንደሆነ ይገለጻል፡፡

በሌላ በኩል በወቅቱ በኢትዮጵያ ሶማሌ፣ በጅቡቲ እና በሶማሌ አገራት መካከል ምንም ዓይነት ድንበር ባለመኖሩ፣ ኢሳዎች ያሉበት መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥም ተያያዥነት ያለው በመሆኑና በአንድ አስተዳደር ሥር ስለነበሩ በፍትሀዊነትና በእኩልነት ሊያስተዳድራቸውየሚችል ህግ ማውጣት አስፈላጊና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ የነበረ መሆኑየኢሳ ሶማሌ አባቶች ሌላኛው ምክንያት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

በባህላዊ ህጉበማኅበረሰቡ ዘንድ የሚፈጸሙ በደሎችን ወይም ከሌላ አካል የሚፈፀምባቸውን ችግሮችለመከላከል እንዲቻል በአጠቃላይ 4 ነገሮችን በዋናነትለመከላከል አሰቀምጠዋል፡፡

እነዚህም 1.የራስ ያልሆነን ሀብትና ንብረት አለመፈለግ፣

2. ወረራ፣

3. ቅሚያ ወይንም ዝርፊያ እና

4. ግድያ ናቸው፡፡

ከዚህም አንጻር ለኅብረተሰቡ ተገቢውን ጥበቃ ለማድረግና ለመከላከል ሲባል የተጠቀሱትን ችግሮች መነሻ አድርጎ ህጉ ትኩረት ያደረገባቸው ጉዳዮችየሚከተሉት ናቸው፡፡ ከደም አፋሳሽ ተግባር ከመቆጠብ፣ የምጣኔ ሀብታዊ ተግባራትን ሁሉንም የኅብረተሰብ ዓካል ፍትሀዊ ተጠቃሚ ከማድረግ፣ እንዲሁም የማንኛውንም ሰው ክብር ካለመንካት፣ የራስን ባህልና ወግ ከመጠበቅና ከመንከባከብ እንዲሁም ከመሬት ጋር በተያያዘ የሰውንም ድንበር ሳይገፉ የራስንም እያስጠበቁ ከመኖር በአጠቃላይ የሥነምግባር ግድፈት ያላቸውን ሰዎች ከመምከርና ከመመለስ አንጻር የተቃኘ ነው፡፡

የኢሳ ሶማሌባህላዊ ህግ የራሱ የመተግበሪያ ቦታ ወይንም ሥፍራ አለው፡፡ የመተግበሪያ ቦታው እንደችግሩ ወይንም ግጭቱ ቅለትና ክብደት የሚወሰን ሆኖ በሁሉም ቦታዎች ማለትም በገጠርም በከተማም እንደፍርድ ቤት የሚገለገሉባቸው የዛፍ ጥላዎችናወንዞች (በተለይ የደም ካሳ ለመፈጸም የሚገለገሉባቸው የወንዞችዳርቻዎች) ዋነኛ የመተግበሪያ ቦታዎች ናቸው፡፡ በከተማዎች አካባቢ ደግሞ ጌድካ ነበዳ ወይም የሰላም ዛፍ የተሰኙ ዘመናዊ አዳራሾች በቅርሱ መተግበሪያ ሥፍራነት ያገለግላሉ፡፡

በማኅበረሰቡ ውስጥ ከላይ እንደስጋት የተለዩ ችግሮችና ወንጀሎች ሲከሰቱ እንደጥፋቱ ቅለትና ክብደት በህጉ የተቀመጡ የቅጣት ደረጃዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ቀላል ጥፋቶችና ግጭቶች ሲከሰቱ በየአካባቢው ባሉ የዛፍ ጥላዎች ወይንም በማኅበረሰቡ አጠራር ፍርድ ቤቶች በሚሏቸው ቦታዎች ላይ ጉዳዮቹ ታይተው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡ ከባድ ወንጀሎች ለምሳሌ ግድያ ከሆነ የደም ካሳ በወንዝ መሀል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

እነዚህ የመተግበሪያ ቦታዎች የማኅበረሰቡ የእርቅ ሥርዓት መፈጸሚያ ቦታዎች ናቸው ብሎ መውሰድም ይቻላል፡፡ በኢሳ ሶማሌማኅበረሰብ በማንኛውም ሁኔታ ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ህይወት መጥፋት የለበትም የሚል ጽኑ እምነት አለ፡፡ ይሁንና በተለያየ ምክንያትና አጋጣሚ የሰው ህይወት ያጠፋ ግለሰብ በባህሉ መሠረት የሚዳኝበትና ሰላም የሚወርድበት የእርቅ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ ለምሳሌ የወንድ ልጅ ህይወት ያጠፋ 100 ግመሎችን በካሳ መልክ ይከፍላል፡፡ ሴት ልጅን የገደለ ደግሞ 50 ግመሎችን በመቀጣት የተበዳይ ቤተሰቦችን ይክሳል፡፡ ካሳውን የሚከፍለው ገዳዩ ብቻ ሳይሆን የገዳዩ ጎሳ በሙሉ ነው፡፡ የአከፋፈሉ ሂደት የገዳይና የሟች ቤተሰቦች ወደ ወንዝ ወርደው ለወራት በመቀመጥ የግመሎቹ ጤና እየተመረመረ የሚረካከቡበት ነው፡፡ የገዳይ ቤተሰብ ወንዝ ወርደው የተጣለባቸው ቅጣት እስኪሟላ ድረስ የሟች ቤተሰቦችን የመመገብ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተሟልቶላቸው ከተረካከቡ በኋላ ለማረጋገጫ ፍየል ያርዳሉ፡፡ ይህ ሥርዓት መከናወኑ የገዳይ ወገን የተጣለባቸውን ቅጣት ያሟሉና ግዴታቸውን የተወጡ ስለመሆናቸው ምልክት ነው፡፡

ኢሳ በሶማሌ ሕዝብ ታሪክ ውስጥ ሠፊ ቦታ ያለው ነው፡፡ በጎሳ ደረጃም 12 (አሥራ ሁለት) ጎሳዎች ያሉት የማኅበረሰብ ክፍል ነው፡፡ የማኅበረሰቡ መነሻ ግን 3 (ሦስት) ጎሳዎች ናቸው፡፡ እነዚህም ዳሎል፣ አብጋልና ወርዲቅ ናቸው፡፡ እነዚህ 3 (ሦስት) ጎሳዎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ልጆች በመውለዳቸው 6 (ስድስት) ሆኑ፡፡ እነዚህም ሆሌ፣ ሀውላቃዴ፣ ኤሌዬ፣ ወርዲቅ፣ ሆሮኔ እና ኡርዊኒ የተባሉ ናቸው፡፡ እዚህ 6 (ስድስት) ጎሳዎችም እንዲሁ እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ልጆችን በመውለዳቸው ብዛታቸው 12 (አስራ ሁለት) ሆኑ፡፡ ከዚህ በመነሳት ነው የኢሳ ማኅበረሰብ 12 (አሥራ ሁለት) ጎሳ አለው የሚባለው፡፡

የኢሳ ማኅበረሰብ የትም ቢኖር አንድ ነው፡፡ አንድ የጋራ ኡጋስ ወይንም መሪ አለው፡፡ ኢሳ እንደሌሎች ሶማሌዎች በገራድና ሱልጣን አይወከልም፡፡ ያለው አንድ ኡጋስ ነው፡፡ ኡጋሱ ወይንም መሪው በየአካባቢው እንደ መንፈሳዊ አባት የሚቆጠር ነው፡፡ የኡጋሱ ሥልጣን በዘር የሚተላለፍ አይደለም፡፡ በኢሳ ህግ ኡጋስ ለመሆን በዚህ አገር አቀፍ ምዝገባ ሰነድ (ኢንቬንቶሪ) ከታች እንደቀረበው የራሱ የአመራረጥ ሥርዓትና ህገ ደንብ አለው፡፡ ኡጋሱከማኅበረሰቡ ወጣት ትውልዶች መካከል በፍሊጋ ተመርጦ በፖለቲካዊ መሪነትና በመንፈሳዊ አባትነት ወደመንበረ ስልጣን የሚመጣ ነው፡፡ የኡጋሱ የአስተዳደር ማዕከል ወይንም መቀመጫ በኢትዮጵያ ድሬዳዋ ከተማ ነች፡፡ ድሬዳዋ ከተማ እስካሁን ድረስ ለነበሩ ኡጋሶች ወይንም መሪዎች መቀመጫ እንደነበረችና አሁንም እንደሆነች የማኅበረሰቡ አባቶች ይናገራሉ፡፡

የኢሳ ሶማሌ ባህላዊ ህግ (Xeer Ciise- ሄር ኢሴ) በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የተደነገገ ነው፡፡ ስድስቱ ዋና ዋና ክፍሎች 160 አንቀጾች፣ 336 ንዑስ አንቀጾች እና 444 መመሪያዎች አሉት፡፡ በድንጋጌው መሠረት የኡጋሱ አመራረጥ የማኅበረሰቡን ባህል በጠበቀ መልኩ የሚከናወን ነው፡፡ ይህም በህጉ ከተቀመጡስድስት ዋና ዋና አንቀጾች መካከል በአንዱ የተመላከተ ነው፡፡ ስድስቱ ዋና ዋና አንቀጾች የሚባሉት የደም (kabtadhiga) ወይንም የነፍስ ግድያ ማለትም የአካል ጉዳት ፍርድ የሚሰጥበት በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ዲግ›› የተባለው፣የኢኮኖሚ (kabta dhaqaalka)፣ የሰብዓዊነት (kabtadheerta) ወይንም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እንዳይኖር ጥበቃ የሚደረግበት በብሔረሰቡ አጠራር ‹‹ዴር››፣ የባህል (kabtadhqanka) ወይንም የማኅበረሰቡ ባህልና ወግ የሚጠበቅበት በብሔረሰቡአጠራር‹‹ደቀን››፣ አብሮት ለሚኖር ህበረተሰብ (kabta dhiblaha)፣ እና የመሬት ጉዳዮች(kabtadhulka)የሚታዩበት ‹‹ዱል››እና ለሌሎች በአካባቢው ለሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች ከለላ ማድረግን የተመለከቱ አንቀጾች ተካተውበት የተደነገጉ ናቸው፡፡

በዚህ መልኩተቀርጾ ከትውልድ ወደትውልድ እየተሸጋገረ የመጣው እና ህጋዊሰውነት ያለው ባህላዊ ህግ ወይንም ሔር ኢሴ የማኅበረሰቡን የዕለት ተዕለት የህይወት እንቅስቃሴና የኑሮ መስተጋብር ሰላማዊ እንዲሆን እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቀጠናውና በድንበር አካባቢዎች የሚከሰቱ ከቀላል እስከ ከባድ የሚደርሱ ችግሮችና ወንጀሎችን በተቀመጠው ህግና ሥርዓት መሠረት ችግሮቹ ስር ሳይሰዱ በፍትኃዊነት እየዳኘና እርቀ ሰላም እያወረደ ማኅበረሰቡ ወደቀድሞ ሰላሙ እንዲመለስ እያደረገ ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል አላስፈላጊ ግጭቶችንና ወንጀሎችን በመቀነስ ረገድምመደበኛውን ህግ በከፍተኛ ሁኔታ እያገዘና እየደገፈ ይገኛል፡፡

በኢትዮጵያ ህገ መንግስት መሠረት የሃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች ሊመሰረቱ እንደሚችሉና እውቅና ሊሰጣቸው እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ለአብነትም በባህል ህግ ሥርዓት ላይ ተመስርቶ ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ መሆኑ፣ የግልና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖትና በባህል ህጎች መሰረት የሚዳኝ መሆኑ ከሚጠቀሱት ህገ መንግስታዊ መሠረቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የኢሳ ሶማሌ ባህላዊ ህግ ህገ መንግስታዊ መሰረቶች ያሟላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በባህላዊ ህጉ የዳኝነት ሥርዓት ላይ ሴቶች ተሳታፊ ባይሆኑም ህጉ ለሴቶች ከፍተኛ ትኩረትና ክብር የሚሰጥ ነው፡፡ በሴቶች ላይ ለሚደርሱ ጥቃቶችና ወንጀሎች ህጉ ከፍተኛ ቅጣት አስቀምጧል፡፡ በተቀመጠው ህግ መሠረትም ቅጣቱን ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ በኢሳዎች ዘንድ ሴቶች ባራአድ፣ ቢላአድ፣ ገምቦአድ እና ሐይን ጎግላ በሚል ተከፋፍለው የሚጠሩበት ስያሜ አላቸው፡፡ ባራአድ ማለት ልጃገረድ ወይንም ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰች ሴት መጠሪያ ነው፡፡ ይህችን ሴት የደፈረ ግለሰብ በባህላዊ ህጉ መሠረት 16 ሴት ግመሎችን ይቀጣል፡፡ ከዚሁ ጋር ግለሰቡ ከማኅበረሰቡ የተገለለ እና ሌላ ሴት እንዳያገባ ይከለከላል፡፡ ለዚህ ግለሰብ ሴት ልጁን የዳረ ሰውም 12 ግመሎች እንደሚቀጣ ህጉ አስቀምጧል፡፡ ይህ በመሆኑም ግለሰቡ በዚህ ድርጊቱ ከማኅበረሰቡ ጋር ጤናማ ማኅበራዊ ህይወትን መኖር ስለማይችል አካባቢውን ለቆ እንዲሰደድ ምክንያት ይሆንዋል፡፡ቢላ አድ የተባለችው ደግሞ የታጨች ሴት መጠሪያ ሲሆን የታጨች መሆኗ እየታወቀ የደፈራት ግለሰብ 15 ግመሎችን እንዲቀጣ ህጉ ያዛል፡፡ ገምቦ አድ የምትባለው ደግሞ ባል የሞተባት ሴት መጠሪያ ነው፡፡ ይህችን ሴት ባል በሞተባት በ4 ወር ከ10 ቀን ጊዜ ውስጥ የደፈራት ሰው 15 ግመሎችን እንዲቀጣ ህጉ ይደነግጋል፡፡ የዚህ ግለሰብ ቅጣት የተጠቀሰውን የግመል ቁጥር ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ሴቶች ጋርም ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳይኖረው ህጉ ይከለክላል፡፡ይህ በመሆኑም እነዚህን መሰል ወንጀሎች ብዙም አይታዩም፡፡

በሌላ በኩል ህጉ ለሴቶች ብቻ ሳይሆን የህጻናት ደህንነትን ከማስጠበቅና ሊደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን አስቀድሞ ከመከላከል አኳያ የተለያዩ ሕጎች የተደነገጉበት ነው፡፡ ለምሳሌ ሴት ልጅ ትንሽም ትሁን ትልቅ አትገደልም፤ ህጻናትም ራሳቸውን መከላከል ስለማይችሉ አይገደሉም፡፡ ከዚሁ ጋር ከህጻናት ጋር በተያያዘ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 36 ላይ ስለህጻናት መብት ጥበቃ የተደነገጉ ሕጎች አሉ፡፡ ድንጋጌውም ህጻናት በአካላቸው ላይ ከሚፈጸሙ ከጭካኔና ከኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች ነጻ የመሆን መብት እንዳላቸው የሚገልጽ ነው፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ከባህላዊ ህጉ ጋር የሚዛመዱ ቢሆኑም በባህላዊ ህጉ ላይ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠውና ልዩ ልዩ የቅጣት ድንጋጌዎች የተካተቱበት ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የኢሳ ባህላዊ ህግ ወይንም ሔር ኢሴ ከመደበኛው ህግ በተሻለ መልኩ በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሱ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን ለመከላከል ብሎም ለማስቀረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እና በማኅበረሰቡዘንድም ለሴቶችና ህጻናት የሚሰጠውን ክብር በዘላቂነት የሚያስጠብቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ከስድስቱ አንቀጾች መካከል የባህል የሚለው አንቀጽ ኡጋሱን በባህሉ መሰረት ለመምረጥ የራሱ ህግና ደንብ የተቀመጠበት አንቀጽ ነው፡፡

ኡጋሱን ለመምረጥ የሚታለፉ ሥርዓት- ሂደቶች አሉ፡፡ በቀዳሚነት ከመጀመሪያ ኡጋስ ጋር ይሰሩ የነበሩ የገንዳ አባቶች ኡጋስ ለሕዝቡ መመረጥ እንዳለበት በመስማማት ይጀምራሉ፡፡ ስምምነታቸውንም ሕዝቡን ሰብስበው እንዲያውቀው ያደርጋሉ፡፡ ከሕዝቡ ውስጥም ኮሚቴ

የሚሆኑ ሰዎችን በመምረጥ በሁሉም ቦታ ለሚኖር የኢሳ ማኅበረሰብ አባላት ኡጋስ እንደሚመረጥ ካሳወቁ በኋላ ሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት በሚገኙበት ከ12ቱ ጎሳዎች የተውጣጡና ማኅበረሰቡን ወክለው የተመረጡ 144 አባቶች ወደዋሩፍ ወይንም ወደጋራ ምክር ቤት የመሰብሰቢያ ቦታ በቀነ ቀጠሮ እንዲሰበሰቡ ይደረጋል፡፡

የእነዚህ የ144 አባቶች የዋሩፍ ላይ ስብሰባሦስት ምክንያቶችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የመጀመሪያው የተጣሉና የተቀያየሙ ሰዎች እንዲታረቁ ማድረግ፣ ከዚህ በተጨማሪ በሁሉም የኢሳ ሶማሌ ማኅበረሰብ ላይ ችግሮች ካሉ መፍታትና ወደቀደመ ሰላማቸው መመለስ ነው፡፡ ሁለተኛው ጸሎት ወይንም ዱአ ማድረግ ነው፡፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው ኡጋሱን መምረጥ ናቸው፡፡ በዋሩፍ ላይ የሚሰበሰቡት አባቶች ከ144 መብለጥ የለባቸውም፡፡ ከ144ቱ አባላት 44ቱ ተለይተው ይመረጣሉ፡፡ 44ቱ አባላት ከላይ እንደተገለጸው ገንዳ ወይንም ሥራ አስፈጻሚ ተብለው ይሰየማሉ፡፡ እነዚህ ገንዳዎች ከኡጋሱ ጋር በቅርበት የሚሠሩና በማንኛውም ጉዳይ ላይ የሚደረስበትን የመጨረሻ ውሳኔ ለኡጋሱ አቅርበው የሚያጸድቁ ናቸው፡፡ እነዚህ አባላት እንደመደበኛው የህግ ሥርዓት የሕገ መንግስት አጣሪ ጉባዔ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ የተቀሩት መቶዎቹ ደግሞ ኡጋሱን ለመምረጥ በኮሚቴነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

እነዚህ አባቶች ወይንም የፓርላማ አባላት የዋሩፍ የስብሰባ ቆይታቸው 4 ወር ከ10 ቀን ነው፡፡ በዚሁ የቆይታ ጊዜ ብዙውን ጊዜ ጸሎት ወይንም ዱአ ያደርጋሉ፡፡ በኢሳ ባህል ለስብሰባ የሚቀመጡ አባቶች ስብሰባቸውን በምርቃት ጀምረው በምርቃት ማጠናቀቅ የተለመደ ሥርዓታቸው ነው፡፡ ምርቃት ወይንም ዱአ በማድረግ የሚጀምረውም ከመካከላቸው በዕድሜ ትልቅ ሳይሆን፣ በኢሳ ጎሳ የበኩር ልጅ የሆነው የ ‹‹ኡረድ›› ጎሣ ዓባል የሆነ ሰው ነው፡፡ ዱአው ካለቀና የተፈጠሩ ችግሮች ከተፈቱ በኋላ 144ቱ አባቶች ኡጋሱን የመምረጥ ሂደቱን ይጀምራሉ፡፡

ኡጋሱ የሚመረጥበት ቦታ በአካባቢው ጌሌ አበሲዬ ወይንም ጉጉማአድ የተባለ ቦታ በመሆኑ አባቶች ወደዚያው ለመሄድ ለዋርዲቅ ሬር ሀሰን (ኡጋስ የሚመረጥበት ጎሳ) ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ወርዲቅ ዩሱፍም በሚይዝላቸው ቀነ ቀጠሮ መሠረት ወደ ጉጉማአድ ከመሄዳቸው በፊት ጊዜያዊ መሪ ከወርዲቅ ሬር ሀሰን ይመርጣሉ፡፡ አያይዘውም ለወርዲቅ ዩሱፍ ለኡጋስነት በመስፈርቱ መሠረት የሚወዳደሩ ወጣቶችን መርጠው እንዲያመጡ ይነግራሉ፡፡ ወርዲቅ ሬር ሀሰን ለዚህ የመረጣ ተግባር ጊዜ ይጠይቁና ወደተለያየ ቦታ ሰዎችን ይልካሉ፡፡ በመጨረሻም የተገኙ ወጣት ልጆችን ስም ከነአያታቸው እንዲሁም የእናታቸውን ጎሳ ቆጥረው ለገንዳ አባቶች ያስረክባሉ፡፡ አባቶችም ‹‹መገንአሌ›› ብለው ይቀበላሉ፡፡ በስም ዝርዝር የመጡ ወጣቶችን ለመለየት በመስፈርትነት የተቀመጠው ከኢሳ ማኅበረሰብ ‹‹ወርዲቅ ሬር ሀሰን›› ከተባለ ጎሳ የተወለደ፣ በአሥራዎቹ የዕድሜ ክልል ላይ ያለ፣ ምንም ወንጀል ያልሠራ፣ ሰው ያልገደለ፣ እንዲሁም በጦርነት ያልተሳተፈ፣ መልከ መልካም የሆነና ከማናቸውም ሱስ የጸዳ መሆን አለበት የሚል ሲሆን፣ እናቱን በተመለከተ ከኢሳ ማኅበረሰብ ከ ‹‹ሰአድ ሙሳ›› የተወለደችና በልጃገረድነት አባቱን ያገባች እንዲሁም ለአባትም መጀመሪያ ባለቤት ወይም ሚስት የሆነች መሆን እንዳለባት ያስቀምጣል፡፡

እነዚህን መሥፈርት ያሟላ ወጣት ሲገኝ አዲሱ ኡጋስ መሆኑን ከተስማሙበት በኋላ ከቤተሰቦቹ ጋር በመነጋገር በሁለተኛው ቀን የኡጋሱ ቤተዘመድ የሆነና ወርዲቅ ዩሱፍ የሆኑት ኡጋሱን ለ‹‹ ሰኢድ ሙሴ›› ሬር ጉለኔ›› ያስረክባሉ፡፡ እሱም ኡጋስ ከይርሌ ወይንም ‹‹የተባረከ ንጉስ›› ይለዋል፡፡

ከዚህ ሂደት በኋላ ኡጋሱ መሬት ላይ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ የሚቀመጥበትን ጉንደቱ ወይንም ምንጣፍ ጨርቅ ‹‹ሀሰን ጋዲድሼ›› የተሰኘ ሰው እንዲያነጥፍ ይደረጋል፡፡ጥምጣሙን ደግሞ ወርዲቅ ዩሱፍ ያለብሰዋል፡፡ ከዚህ ሥርዓት በኋላ በሰፊው ዱአ ተደርጎ በማግስቱ ጠዋት ወደ 144ቱ አባቶች ወደተቀመጡበት ቦታ ወደዋሩፍ ጉዞ ይጀመራል፡፡ እዚህ ቦታ እስኪደርስ ድረስ ሕዝቡ በየቦታው እየወጣ በእልልታና በባህላዊ ጭፈራ ይሸኘዋል፡፡ ‹‹ጉጉማአድ›› ሲደርስ አባቶች በፍቅር ተቀብለው ምርቃት ያደርጉለታል፡፡ እዚህም ቦታ በህጉ መሠረትሰባት ቀን እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ ይህ ሥርዓት ሂደት እስኪጠናቀቅ ድረስ የሚቀመጥበትን ጉንደት ወይንም ምንጣፍ የሚያነጥፍለት ሁል ጊዜ ‹‹ሀሰንጋዲድሼ›› የሆነ ሰው ሲሆን ይህ ሰውም ከኋላው የሚቀመጥ ነው፡፡ እዚህ ቦታ እስካለ ድረስ ሕዝቡ (የማኅበረሰቡ አባላት) ከያሉበት እየመጡ የተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎችን እየጨፈሩና እየተጫወቱ የኡጋሱን እጅ በክብር እየሳሙ ምርቃት ያደርጉለታል፡፡

ከሰባት ቀን ቆይታ በኋላ ኡጋሱ ወደ ሚሌ ይወሰዳል፡፡ ሚሌ እና ጉጉማአድ የ5 ኪ.ሜ. ልዩነት አላቸው፡፡ ጉጉማአድ ደርሰው ካረፉ በኋላ 144ቱ የኢሳ አባቶች ለወርዲቅ ሬር ሀሰን ኡጋሱን ለ40 ቀን ያህል በአደራነት ያስቀምጣሉ፡፡ ሲያስቀምጡም እንዲህ በማለት ነው፡፡ ‹‹ሬር ሀሰን ሆይ ታላቁ ኢሴ ከዛሬ በኋላ ኡጋሱን ለ40 ቀን በአደራነት እናንተ ጋር አስቀምጠዋል›› ሬር ሀሰንም ‹‹ተቀብለናል ከአላህ ጋር እኛ ጋር ይቆያል›› ይላል፡፡ ከዚህ ሂደት በኋላ 144ቱ አባቶች ወደየቤታቸው ይሄዱና በቀጠሮው ቀን ከ40 ቀን በኋላ በመምጣት ይዘውት

ሌላው ሂደት ይጀመራል፡፡ ኡጋሱ ሰይላ እስኪወስድ ድረስ ለ6 ወራት ያህል ገጠር ውስጥ እንዲቆይና ወደ ሁሉም የኢሳ መሬቶች እንዲጓዝ ይደረጋል፡፡

በህጉ መሰረት በኡጋስ መረጣው ስራ በሚደረጉ ልዩ ልዩ ተግባራት የተለያዩ የካሳ ክፍያዎች አሉ፡፡ ለአብነት ጥምጣሙን የሚያለብሱት ወርዲቅ ዩሱፍ ሲሆኑ ጥምጣሙን ባለበሱበት ጊዜ 100 ትንንሽ ፍየሎች ይሰጣቸዋል፡፡ ለኡጋስነት ለውድድር የቀረቡና በየቤታቸው እየተሄደ የታዩ ወጣቶች ደግሞ አንድ አንድ ትንሽ ሴት ግመል ይሰጣቸዋል፡፡ የኡጋሱ ቤተሰቦችም የልጁ ካሳ ይከፈላቸዋል፡፡ ምክንያቱም ከዚያን ቀን ጀምሮ ልጁ የኢሳ ልጅ እንጂ የእነሱ አይደለም፡፡ የሚጠብቀውም በህጉ መሠረት ኢሳ ኅብረተሰብ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡

በሌላ በኩል ለኡጋሱ ክብር የሚደረጉ የስጋና ወተት ሥርዓተ ሂደቶች ( አኖ ኢዮ አዲን) አሉ ፡፡ ለክብሩ ሲባል ከተመረጡ የግመል፣ የላምና የበግ ዘሮች የታለበ ወተት እንዲጠጣ ይደረጋል፡፡ በየሄደበትም ደግሞ ከሁሉም ዓይነት እየታረደለት ከሕዝቡ ጋር አብሮ ይበላል፡፡ የኡጋሱ የወተትና ስጋ ሥርዓት- ሂደት ካላቀ በኋላ ጉዞውን ወደ 12ቱ ወንዞችና ኡጋስነቱን የመቀበል ሥነ-ሥርዓቱ ወደሚጠናቀቅበት ወደ ሰይላእ ወይንም ዘይላ ከተማ ያደርጋል፡፡ 12ቱን ወንዞች የሚያልፈው በባዶ እግሩ ነው፡፡ 12ቱ ወንዞች በሁለት የተከፈሉ ናቸው፡፡ 6ቱ አሸዋማ፣ ሲሆኑ 6ቱ ደግሞ ጭቃማ ናቸው፡፡ 6ቱ አሸዋማ ወንዞች ኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆኑ፣ 6ቱ ጭቃማ ወንዞች ደግሞ በጅቡቲና ሶማሌ ላንድ ውስጥ የሚገኙ ናቸው፡፡ይህን ሂደት ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ሰይላእ ወይንም ዘይላ ተወስዶ ሰባት ቀን የቀይ ባህር ውኃ ውስጥ እግሩን ካስገባ በኋላ በ8ኛው ቀን ኡጋስነቱን የመቀበል ሥነ-ሥርዓት ይጠናቀቃል፡፡ የንግስና ወይንም ኡጋስነት የመቀበል ሥነ-ሥርዓቱ የሚጠናቀቀው ወርዲቅ ሬር ዩሱፍ ኢማመቱን ወይንም ጥምጣሙን ካለበሱት በኋላ ነው፡፡

የኡጋሱ የሥልጣን ጊዜ የዕድሜ ልክ ነው፡፡ ይሁንና ኡጋሱ በስልጣን ቆይታው የተመረጠበትን ዓላማ ማሳካት ካልቻለ ወይም ሥልጣኑን አላግባብ ከተጠቀመ የመረጠው ማኅበረሰብ እንዳስቀመጠው ሁሉ ያወርደዋል፡፡ የኡጋሱ ስልጣን ዘውድ ወይንም ክራውን እንደሚባለው በኢሳ ህግ ጥምጣሙ ‹‹እማማው›› ነው፡፡ ስለዚህ ወደ ሥልጣን ሲወጣ ወይንም ሲነግስ እማማውን እንደሚያለብሱት ሁሉ ከስልጣን በሚወርድበት ጊዜ ደግሞ ጥምጣሙን ቀምተው ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ሌላ ኡጋስ ይመርጣሉ፡፡

በአጠቃላይ የኢሳ ማኅበረሰብ ባህላዊ ህግ ወይንም ሔር ኢሴ በማኅበረሰቡ ዘንድ የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው የእያንዳንዱ ትውልድ አሻራ እየታከለበት ከትውልድ ወደትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ፣ የማኅበረሰቡን አባላት በእኩልነት በማስተዳደር የዕለት ተዕለት ህይወታቸውና መስተጋብር በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲገነባ፣ በባህሉ የማይደራደርና የሚኮራ ትውልድ የፈጠረ እና እየፈጠረ ያለ መደበኛውን ህግ የሚያግዝ እንዲሁም ለሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች የአብሮነት ህይወትንና ወንድማማችነትን የሚያስተምር ብሎም በቀጠናው ዘላቂ ሰላምን በመፍጠር ረገድ የፍትኃዊነት፣ የእኩልነትና አብሮ የመኖርና የመልማት አስተምህሮት ያለው የማኅበረሰቡ ህያው ሀብት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

### 2.3 የቅርሱ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ (significance of the intangible cultural heritage)

የኢሳ ማኅበረሰብ ባህላዊ ህግ ሃይማኖትንም ሆነ መደበኛውን ህግ በማይጻረር ይልቁንም ባጣማ መልኩ የተዘጋጀና በማኅበረሰቡ የጋራ ስምምነትና ይሁንታ የጸደቀ፣ ግልጽ አሠራርን ተከትሎ የሚፈጸምና በፍትኃዊነትና በእኩልነት ማኅበረሰቡን የሚያገለግል በመሆኑ ለማኅበረሰቡ የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

ባህላዊ ህጉ የኢሳ ሶማሌ ማኅበረሰብ መገለጫ ቢሆንም ሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች አብሮ ከመኖርና እንደራሳቸው ባህል ከመልመዳቸው አኳያ እየተዳኙበትና በሥርዓቱ ላይ እየተሳተፉበት እንዲሁም ከለላም ሆኖ እያገለገላቸው ይገኛል፡፡ ይህ ደግሞ በአካባቢው ለሚኖረው ማኅበረሰብ ሰላማዊ ህይወትን በማስፈን ወንድማማችነትንና አብሮነትን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው፡፡

ህጉ የርስበርስ ሰላምን ከማረጋገጥ አንጻር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች አጎራባች ክልሎችና የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ሊያጠናክር በሚችል መልኩ የተደነገገ በመሆኑ ከአካባቢው አልፎ ለቀጠናው ሰላም መረጋገጥ የህልውና መሠረት ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሦስቱምአገራት ማለትምበጅቡቲ፣በሶማሊ እና በኢትዮጵያ ያሉ የኢሳ ሶማሌ የማኅበረሰብ አባላት በያሉበትና በሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ በአንድ ኡጋስ የሚመሩናበባህላዊ ህጉ አሠራር በእኩልነትና በፍትኃዊነትተጠቃሚበመሆናቸው ባህላዊ ህጉ ይበልጥ የሚያስተሳስራቸው፣ የሚያቀራርባቸውና አንድነታቸውን የሚያጠናክሩበት በመሆኑ ጠቀሜታው ዘርፈ ብዙ ነው፡፡

ከዚህ ሌላ የማኅበረሰቡ አባላት በዕለት ተዕለት የህይወት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ በሚፈጥሯቸው መስተጋብሮች የሚፈጠሩ ችግሮች ስር ሳይሰዱ እልባት በመስጠት የሚዳኝና አሸናፊና ተሸናፊ ሳይኖርበት ወደቀደመ ሰላማቸው የሚመልስ በመሆኑ ለማኅበረሰቡ አባላት የሰላም ዋስትና ሆኖ እያገለገለ ይገኛል፡፡

በሌላ በኩል ባህላዊ ህጉ መደበኛውን ህግ በማገዝና ከቀላል እስከ ከባድ የሚደርሱወንጀሎችን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ነው፡፡ በተለይ ለሴቶች የሚሰጠው ከፍተኛ ትኩረትና ክብር ለሌሎች የማኅበረሰብ ክፍሎች እንደተሞክሮ የሚወሰድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባህላዊ ህጉን ከማዘጋጀት እስከ ትግበራ ባለው ሂደት ውስጥ በየደረጃው ያሉ ወንዶች የሚሳተፉበት በመሆኑ በተለይ ተተኪው ትውልድ የሆነው ወጣት ለባህላዊ ህጉ ተገገር፣ ህጉን አክባሪ፣ አስቀጣይና ፍትኃዊ ተጠቃሚ እንዲሆን በማስቻል ረገድ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ የቅርሱ ትግበራ ከታች ከግለሰብ ጀምሮ እስከ በላይ አስፈጻሚ ድረስ የተስማሙበት ውሳኔ ያለልዩነት ሁሉም እንዲያውቀው ተደርጎ የሚተገበር በመሆኑ በማኅበረሰቡ ዘንድ እኩል እምነትንና ግልጽ አሠራርን ማስፈን ያስቻለ ነው፡፡ ይህምሁኔታ ማኅበረሰቡ በባህላዊ ህጉ እኩል ተገልጋይና ተጠቃሚ እንዲሆን ያስቻለ በመሆኑ ጠቀሜታው ሁለንተናዊ ነው፡፡

## 3. **የቅርሱ መለያ ባህርያት** (Characteristics of the element)

### 3.1 **የቅርሱቁሳዊመገለጫ** (Associatedtangible aspects)

በባህላዊ ህጉ የአፈጻጸም ሥነ- ሥርዓት ላይ የተለያዩ ቁሳዊ መገለጫዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ከቁሳዊ መገለጫዎቹ መካከል ጥላ ያላቸው የመተግበሪያ ሥፍራ ዛፎች፣ መቀመጫ ድንጋዮችና ወንዞች ዋናዎቹ መገለጫዎች ሲሆኑ ከአለባበስ ጋር በተያያዘ የኢሳ ማኅበረሰብ አለባበስ በማንኛውም ዐውድ ላይ የተለየ አይደለም፡፡ የዘወትርም ሆነ የሽምግልና ሥርዓት አለባበሱ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም ከወገብ በላይ ነጭ ካኒተራ ወይንም ቲሸርት፣ ከወገብ በታች ደግሞ ጉንደቱ (ነጭ ግልድም ወይንም ሽርጥ መሀሉ ላይ ጥለት ያለው) ይለብሳሉ፡፡ ወገባቸው ላይ ደግሞ ጉንዴቱውን ወይንም ግልድሙን ለማሠርና ለማጥበቅ ከላም ቆዳ የተሠራ ቀበቶ ይታጠቃሉ፡፡ ከዚህ ሌላ ትንሽ ዱላ ይይዛሉ፡፡ ጊሌ (ባህላዊ ቢላዋ) በወገባቸው ላይ ያደርጋሉ፡፡ መጫሚያን በተመለከተ ግራና ቀኝ የሌለው ከላም ቆዳ የተሠራ ጫማ ይጫማሉ፡፡ ትከሻቸውም ላይ ትንሽና ስስ ኩታ ጣል በማድረግ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ይታደማሉ፡፡ በሌላ በኩል በግጭት አፈታት ሥነ-ሥርዓቱ ላይ እንደወንጀሉ ክብደትና ቅለት በህጉ ተወስኖ የተቀመጠውና በቅጣት መልክ ለተጎጂ ወይንም ተበዳይ በካሳ መልክ የሚቀርበው የግመል ብዛት ሌላው የቅርሱ ቁሳዊ መገለጫዎች ሆነው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ሌላው ደግሞ ለኢሳ ማህበረሰብ ብቻ የሚያገለግል ልዩ ምልክት እያንዳንዱ የኢሳ ክፍል አለው፡፡ ይህንንም በማንኛውም እቃ ወይም ሀበታቸው ላይ ማለትም ከበቶቻቸው ላይ ግመሎች ፤እንዲሁም ፍየሎቻቸው ላይ ያደረጉታል፡፡ ይህም ንብረታቸው እንዳይጠፋባቸውና ከተገኘም እንዲመለስላቸው ይረዳቸዋል፡፡

### 3.2 **የቅርሱ አካላዊ መገለጫ** (Associated intangible aspects)

በኢሳዎች ዘንድ የተለያዩ ከቀላል እስከ ከባድ ወንጀሎች ሲፈጸሙ እንደወንጀሉ ቅለትና ክብደት የዳኝነት ሥርዓት ለማከናወንና ለጉዳዩ መፍትሔ ለመስጠት የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና ሥነ-ሥርዓቶች ይኖራሉ፡፡ የዳኝነት ሥነ-ሥርዓቱ በታላላቅ አባቶች ጸሎት ወይንም ዱአይጀመራል፡፡ጸሎት ሲደረግ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የታደሙት ሁሉ በመቆም ሥርዓቱን ይፈጽማሉ፡፡

በኢሳ ማኅበረሰብ የእርቅና የዳኝነትሥርዓት የሚፈጸምበት የተከበረ የማስፈጸሚያ ቦታ አለ፡፡ ይህ ቦታየማኅበረሰቡ አባላት እንደፍርድ ቤት የሚገለገሉበት ጥላ ያላቸው ዛፎች ናቸው፡፡ በዚህ የዳኝነት ሥፍራ ላይ የሚቀመጡት ከ12ቱ የኢሳ ጎሳ የተውጣጡየገንዴ ተወካይ አባላት የሆኑ ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ የገንዴ ተወካይ አባላትና ሌሎች በኮሚቴነት የሚያገለግሉ የየጎሳው ተወካዮች ሥነ-ሥርዓቱን ክብ ሠርተው በመቀመጥ የከሳሽና ተከሳሽ ጉዳይንና የዳኝነት ሂደቱን በህጉ መሠረት ያስፈጽማሉ፡፡ የየጎሳው ተወካዮች የሚቀመጡት ለየጎሳው በመለያነት ምልክት በተደረገባቸው የድንጋይ መቀመጫዎች ላይ ነው፡፡ ከሳሽና ተከሳሽ ግራና ቀኝ በመቆም ጉዳያቸውን

ይከታተላሉ፡፡ ሥነ-ሥርዓቱ በታላላቅ አባቶች ጸሎት ይጀመራል፡፡ከሳሽና ተከሳሽ ወደ ጉዳያቸው ከመግባታቸው በፊት ዋሳቸውን ያቀርባሉ፡፡ ቀጥሎም አንድ ሰው እንደ ጸሀፊ ይመረጣል እያንዳንዱ ሰው አንድ ቃል በተናገረ ቁጥር በመድገም ይናገራል፡፡ ምንም አይነት የቃል ስህተት ወይም አለመረዳት እንዳይመጣ ተናጋሪው ሲጨርስም ያለውን ሀሳብ በመድገም ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል፡፡ በዚህ አይነት ሁለቱም ሰዎች ጉዳያቸውን ያስረዳሉ፡፡ ከዛ ከሳሽ ሀሳቡን በቅድሚያ እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ ተከሳሽ በተከሰሰበት ጉዳይ ላይ መልስ እንዲሰጥ እድል ሲሰጠው ምላሹን ያቀርባል፡፡በጥቅሉ የህጉ አስፈጻሚ አካላት ወንጀል ፈጻሚዎችን በማቅረብ፣ጉዳዩን በመከታተል፣ የከሳሽና ተከሳሽ ቃልን በመቀበል ረገድ የተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ይደረጋሉ፣

በሌላ በኩል የምስክሮች የምስክርነት ቃል ሲደመጥ፣እንደተፈጸመው የጥፋት ሁኔታ የሚጣል ቅጣትን ተከትሎየሚፈጸሙ ሥርዓተ ሂደቶች ላይና በመጨረሻም በከሳሽና ተከሳሽ መካከል እርቅ ሲወርድበልዩ ልዩ መልኩ የሚገለጹ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ፡፡

ለአብነትም ሰላም መፈጠሩን በመተቃቀፍ የመግለጽ፣ አብሮ የመብላት፣ የመጎራረስ፣ በአንድ ዕቃ የመጠጣት በጥቅሉ ልዩ ልዩ ባህላዊ ሥርዓቶችን በመፈጸም ሰላም መውረዱ በተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች ይገለጻል፡፡በሥነ-ሥርዓቱ ማጠናቀቂያም በማኅበረሰቡ ባህልና ወግ መሠረት ሥነ-ሥርዓቱ በጸሎት እንደተጀመረ ሁሉ በታላላቅ አባቶች ጸሎትና ምርቃት ይጠናቃቃል፡፡

4.ምዝገባ (ኢንቬንቶሪ)ከተደረገለት ቅርስ ጋር በተያያዘ ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት፡-

4.1 የቅርሱ ፈጣሪዎች/ተግባሪዎች/አከናዋኞች/Practitioner/s/Performer፡-

የቅርሱ ፈጣሪዎችም ሆኑ ተግባሪዎች በኢትዮጵያ፣ በጅቡቲ፣ በሶማሌ የሚኖሩ የኢሳ ሶማሌ ማኅበረሰብ አባላት ናቸው፡፡

4.2. ሌሎች ተሳታፊዎች/ባለቤቶች/ጠባቂዎች Other participants (custodians)፡-

ለቅርሱ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያደርጉት በዋናነት በሶማሊ ላንድ፣ በጅቡቲ፣በኢትዮጵያ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድርና በድሬዳዋ የሚኖሩ የኢሳ ሶማሌ የማኅበረሰቡ ተወላጆች እና ኡጋሱና የገንዴ አባቶች ወይንም የጎሳ አባላትቢሆኑምየሶማሌ ክልል የባህል ቅርስና ቱሪዝም  ቢሮ፣ ሲቲሄርቴጅ ፋውንዴሽን የተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ፣የክልሉ አስተዳደር እና በየደረጃው የሚገኙ የአስተዳደር አካላት የቅርሱ ጠባቂዎች እና ተሳታፊዎች ናቸው፡፡ባህላዊ ህጉ ትክክለኛ የማኅበረሰቡን ነባር ትውፊት ጠብቆ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር ከቅርሱ ባለቤቶች፣ ግለሰቦችና የባህል ቢሮውእና ሲቲ ሄርቴጅ ፋውንዴሽን ከተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባለፈሌሎች ተቋማት ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በዚህም የባህላዊ ህጉ ትግበራናትውፊታዊ ሥነ-ሥርዓት ተጠብቆ እንዲቆይናበትውልዶች ቅብብል እንዲጎለብትህጻናትና ታዳጊዎችን በጽንሰ ሀሳብ እና በተግባር በማስተማር የቅርስ ተቆርቋሪ ትውልድ እንዲፈጠር በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

4.3. ቅርሱን ለማየት ወይም ለመድረስ ያሉ ሥርዓቶችና ደንቦች /Customary practices governing access to the element or to specific aspect of it/:-

በተግባር ዳኝነቱን ከማስፈጸም አኳያ ሙሉ በሙሉ የወንዶች ኃላፊነት የነበረ ቢሆንም ባህላዊ ህጉን ከማዘጋጀት ጀምሮ ሴቶች የራሳቸውን አስተዋፅኦ አድረገዋል፡፡ባህላዊ ህጉ በሚረቀቅበትም ጊዜ በቦታው ከ44 ወንዶች ጋር የተሳተፈችው ብቸኛዋ ሴት ነበረች፡፡ በህጎቹም ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርጋ በተለይ ሴቶችን በተመለከተ በሚደነገግበት ጊዜ ህጎች ላይ በአብዛኛው የርሷ ሀሳብ እና አስተያየት የታከለበት ነበር፡፡ ሴቶችም በሴቶች መሀል ችግር ሲፈጠር ወደ ወንዶች ከመሄድ ይልቅ ሴቶች እራሳቸው ተሰባስበው ችግሮቹን ለመፍታት ይሞክራሉ፡፡ ሴቶች በባህላዊ ህጉ ላይ ትኩረት የተሰጣቸው ቢሆንም ቀጥተኛ ተሳትፎ የላቸውም፡፡ ከዚህ ውጪ ባህላዊ ህጉ በእኩልነት የሚገለገሉበት በመሆኑ በተለየ ሁኔታየቅርሱን ክዋኔ ለማየት፣ ለመድረስ ወይም ለመከወን የተጠቀሰ ምንም አይነት ገደብና ክልከላ የሌለው መሆኑን አስረጂዎች ገልጸዋል፡፡

5. የቅርሱ ቀጣይነትና ደህንነት፡-

5.1. ቅርሱ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ/ current status of the element/:-

የኢ.ሳ ማኅበረሰብ ባህላዊ ህግ የማኅበረሰቡ አባላት የረጅም ጊዜ የማንነት መገለጫና ታሪክ ነው፡፡ ባህላዊ ህጉ በየዘመኑ ያለው ትውልድ የራሱን አሻራ እያከለበትና እየተቀባበለው ለህጉ ተገዢ በመሆንና በማክበር ሲገለገልበት የኖረ የማኅበረሰቡ እሴት ነው፡፡ በሦስቱም አገራት የሚገኙና የሚኖሩ የማኅበረሰቡ አባላት በወቅታዊና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ በመሰባሰብ በመምከር ለተፈጠሩ ጊዜያዊ ችግሮች መፍትሔ በመስጠትና ባህላዊ ህጉንለማጠናከር የመረጃ ልውውጥያደርጋሉ፡፡

ባህላዊ ህጉ እንደመደበኛው ህግ የማሻሻያ ደንብና ሥርዓት ባይኖረውም ህጉ በየጊዜው እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ በዚህም ሂደት ከአያት ቅድመ አያቶቻቸው የተቀበሏቸውን ህጎች ከማስፈጸሙ ጎን ለጎን ከጊዜው ጋር የማይሄዱትንና ለኅብረተሰቡ ማኅበራዊ፣ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መንፈሳዊ ሕይወት  እንቅፋት የሆኑ ነባር ህጎች እንዲሻሻሉና ከአድሎና ከኢ-ፍትኃዊ አሠራር በራቀ መልኩ የተዘጋጁአዳዲሶችም እንዲወጡ፣ እንዲታወቁና ስራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ የኅብረተሰቡ ሁለንተናዊ ህይወት እንዲሳለጥ ይሰራሉ፡፡በዚኅ ጉዳይ ላይ የተቀመጠው የህግ አንቀጽ አለው፡፡ አንቀጹም እንዲህ ይላል‹‹xeerku waa wax la sugay iyo wax la sugaayo ›› ማለት ‹‹ይህ ህግ የተደነገገና የሚደነገግ ነው›› ለማለት የተፈለገውም ዋናው ምክንያት መጨመር ወይም ማሻሻል እንደሚቻል ነው፡፡በዚህ ምክንያት ማኅበረሰቡ ከመደበኛው ህግ ይልቅ በባህላዊ ህጉ መዳኘት ይፈልጋል፡፡ በተለይ በገጠር የሚኖረው ማኅበረሰብ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በባህላዊ ህጉ የሚገለገል ነው፡፡ በከተማም ቢሆን ከመደበኛው ህግ ጎን ለጎን በአብዛኛው በባህላዊ ህጉ ይገለገላል፡፡ ከዚህ በመነሳት ቅርሱ አሁንም በከፍተኛ ሁኔታ እየተተገበረ የሚገኝ የማኅበረሰቡ ህያው ሀብት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

### 5.2. **ቅርሱን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገዶች**/ Modes of transmission from generation to generation፡-

ይህ ቅርስ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ የረዳው እያንዳንዱ አንቀጽ ሲደነገግ በአባባል መልክ ነው የተቀመጠው፡፡ይህም ሕጎቹ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቀላሉ እንዲተላለፉና እንዳይረሱ አድርጓል፡፡የቅርሱ ክዋኔ ትክክለኛ ትውፊቱን በጠበቀ መልኩ ለማስተላለፍ ዋነኛውና ተቀዳሚው ተግባር ማኅበረሰቡ (የጎሳ አባላት) የቅርሱን ሥርዓተ ክዋኔ በትክክለኛው መንገድ እንዲተገብሩት ማበረታታትና ወጣቱ ትውልድ ትውፊቱንና ባህሉን እንዲያውቅ በቅርሱ ትግበራ ሂደት ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡በቅርሱ ዙሪያ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ለቅርሱ ማከናወኛ ባህላዊ ሥፍራዎችበዋናነት ማኅበረሰቡ እንደፍርድ ቤት የሚገለገልባቸው የዛፍ ጥላ ሥፍራዎችንና ወንዞችን ተገቢውን ጥበቃ በማድረግና ከቅርሱ ጋር የተያያዙ ዕውቀቶችን በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በማካተት ለትውልድ የሚተላለፉበትን ሥርዓት መዘርጋትቅርሱን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገዶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻርየጎሳው አባላት በተለይ የገንዴ አባቶች ኡጋሱን ጨምሮ ፣የአገር ሽማግሌዎች ፣አዛውንቶችና የሃይማኖት አባቶች ስለ ቅርሱ ታሪካዊ አመጣጥ፣ የአፈጻጸም ሂደት የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም ለዘመናት ያካበቱትን ዕውቀትና ክህሎት ተተኪው ትውልድ በተለይም ወጣቱን ተሳታፊ በማድረግመቅሰም እንዲችል የበኩላቸውን ድርሻ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ትውፊታዊ ሥርዓቱን በተለያዩ የኅትመትና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ማለትም በቴሌቭዥን፣ በሬዲዮ፣ በጋዜጦች፣ በድረ ገጾች ወዘተ..፣ በመደበኛና ኢ-መደበኛ የመገናኛ መድረኮች ለአብነትም በፓናል ውይይቶች፣ በሲምፖዚየሞች፣ በተለያዩ የምክክር መድረኮች በመጠቀም እየተላለፈ ይገኛል፡፡ከዚህም በተጨማሪ ወቅታዊና አገራዊ የጸጥታ ጉዳዮች ሲከሰቱ ቀጣናዊ ሰላምን ከማረጋገጥ አኳያ የሶስቱም አገራት ተወካዮች በሚገኙበት በሚደረጉ የጋራ ውይይቶችና መድረኮች ባህላዊ ሕጉን ጥቅም ላይ እያዋሉት ይገኛሉ፡፡የቅርሱን እሴቶችና ጠቀሜታዎች በትግበራከማስተዋወቅ ጎን ለጎን፤ በምስል፣ በድምጽና በጽሑፍ ቀርጾና ሰንዶ በማስቀመጥ ለትውልድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ከዚህ ባለፈ የሚመለከታቸው መንግስታዊናእንደ ሲቲ ሄርቴጅ ፋውንዴሽን የመሳሰሉ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችናተቋማት በሙሉ ለቅርሱ ህልውና ቀጣይነት የሚከናወኑ ማናቸውንም ተግባራት በመምራትና በመደገፍ ለባህላዊ እሴቱ ወይም ትውፊቱ ቀጣይነት የላቀ አስተዋጽኦእያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

### 5.3. **ቅርሱን ለመተግበር ያሉ ስጋቶች**/ Threats to the enactment፡-

#### 5.3.1. **አካላዊ /ቁሳዊ ስጋት** (physical threat)፡-

ቅርሱን በመተግበር ረገድ እንደስጋት የሚወሰዱ አካላዊም ሆነ ቁሳዊ ስጋቶች የሉም፡፡ በቅርሱ ትግበራ ወቅት የጎሳው ተወካዮች (የገንዴ አባቶች) በመተግበሪያ ቦታቸው በመሰባሰብ በተፈጠሩ ችግሮች ዙሪያ በህጉ መሠረት በመነጋገርና በመደማመጥ የሚፈቱት በመሆኑ እንደስጋት የሚጠቀስ አካላዊም ሆነ ቁሳዊ ስጋት የለም፡፡

#### 5.3.2. **ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊስጋቶች** (socio-economic threats)

ባህላዊ ህጉ ከመደበኛው ህግ ጋር ተስማምቶ እየተተገበረ የሚገኝ ሲሆን ከኢኮኖሚ አንጻርም አገልግሎቱ ፈጣን ጉልበትን፣ ጊዜንና ወጪን በሚቆጥብ መልኩ የሚሠራ በመሆኑ ማኅበረሰቡን ለተለያዩ እንግልቶችና ወጪዎች የሚዳርግ አይደለም፡፡ ከዚሁ ጋር በዳይና ተበዳይ ህጉ በሚያስቀምጠው አግባብ የሚዳኝ በመሆኑ አሸናፊና ተሸናፊ የማይኖርበት ነው፡፡

ይሁንና ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አሁን ላይ ባህላዊ ህጉ በአግባቡ እንዳይተገበር ዘመናዊነት አንዱ ተግዳሮት እየሆነ መጥቷል፡፡ ለአብነትም የማኅበረሰቡ አባላት በተለይም ወጣቱ ከገጠር ወደከተማ የመግባትና የከተማ ህይወትን የመልመድ ሁኔታ እየታየ በመምጣቱ በተወሰነ ደረጃ ባህሉን የመተው ዝንባሌ እና ለባህላዊ ህጉ ትኩረት የመቀነስ ሁኔታ እየተስተዋለ ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባህሉንና ህጉን በደንብ የሚያውቁ የጎሳው አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ለተተኪው ትውልድ ዕውቀታቸውን ሳያስተላልፉ በማለፋቸው ተተኪው ትውልድ ለባህሉ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ ወደዘመናዊነት እያዘነበለ ይገኛል፡፡ ይሁንና የቅርስ ተቀርቋሪ ግለሰቦች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተለይ እንደሲቲ ሂርቴጅ ፋውንዴሽን ዓይነቶችና የክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና በየደረጃው ያሉ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት የፓናል ውይይቶችንና ሲምፖዚየሞችን በማዘጋጀት ከባህላዊ ሕጉ ጋር የተያያዙ ዕውቀቶችና ክሎቶች ወደ ወጣቱ ትውልድ እንዲተላለፉ በማድረግ እንደ ሥጋት የቀረበውን ችግርለመቅረፍ በከፍተኛ ሁኔታ በትብብር እየሠሩ ይገኛሉ፡፡

### 5.4. ለቅርሱ ቀጣይነት እየተደረጉ ያሉ እንክብካቤዎች/ Safeguarding measures in place፡-

የክልሉ የባህልና ቱሪዝም ቢሮና ሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በተለይም ሲቲ ሂርቴጅ ፋውንዴሽን የተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ባህላዊ ህጉን በማጥናት፣ ዶክመንት በማድረግ፣ ክዋኔውን በምስል በመሰነድና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ማለትም በኅትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች እንዲተዋወቅ በማድረግ ረገድ የተለያዩ የጥበቃና የእንክብካቤ ሥራ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የቅርስ ተቋርቋሪ ግለሰቦች በባህላዊ ሕጉ ላይ በተለያየ መልክ ጥናት በማካሄድና በመሰነድ፣ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን በህጉ ላይ በመሥራት፣ በመጣጥፍና በመጽሐፍ መልክ በማሳተምለባህላዊ ህጉ መጎልበትና ቀጣይነት ብሎም ይበልጥ ተጠቃሚነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱእንደሚገኙ መረጃ ሰጪዎች ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በቱሪዝም ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን ከሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ እና ከሲቲ ሂሪቴጅ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር የኢሣ ማኅበረሰብ ባህላዊ ሕግን በዩኔስኮ የሰው ልጆች ወካይ የማይዳሰስ ባሕላዊ ቅርሰ ዝርዝር ውስጥ በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ እያደረገ ያለው ጥረት ለቅርሱ ቀጣይነት እየተደረጉ ካሉ እንክብካቤዎች መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡

## 6. የመረጃ አሰባሰብና ጥንቅር (Data gathering and inventorying)

### 6.1 በኢንቬንቶሪው ወቅት የኀብረተሰቡ፣ የቡድኖችና ግለሰቦች ተሳትፎ መገለጫዎች (Consent from and involvement of the community/group in data gathering andinventorying)

የኢሳ ማኅበረሰብባህላዊ ህግ ሥርዓት - ክዋኔ የማይዳሰስ ቅርስ ኢንቬንቶሪ በተከናወነበት ወቅት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት፣ ኢንቬንቶሪው የተካሄደበት የሶማሌ ክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች፣ የሲቲ ሂርቴጅ ፋውንዴሽን መስራች አባላት እና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የማይዳሰስ ቅርስ ጥናትና ምርምር ባለሙያዎች በከፍተኛ ኃላፊነትና ተነሳሽነት በኢንቬንቶሪው ላይ ሙሉ ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ኢንቬንቶሪው በተካሄደበት አካባቢ የሚገኙ የአካባቢው የጎሳ አባቶች፣ የኢሳ ሶማሌ የፖሎቲካ መሪና መንፈሳዊ አባት የሆኑት ኡጋስ፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች (ሼሆች)፣እናቶች፣ ወጣቶች፣ ምሁራንና የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ስለ ቅርሱ ምንነት መረጃዎችን ለመሰብሰብ በተደረጉ ቃለ መጠይቆችና የቡድን ውይይቶች ላይ በዋናነት ተሳትፈዋል፡፡

### 6.2ኢንቬንቶሪ የተደረገውን ቅርስ ለመጠቀም ያሉ ገደቦች (Restriction, if any, on use of inventoried data)

በአገርአቀፍ ደረጃ የኢንታንጀብል ወይም የማይዳሰስ ቅርሱን ለማስተዋወቅና ለቅርሱ ባለቤቶች የባህል ዕድገት በሚኖረው ፋይዳ ዙሪያ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና ጥረቶች በግብዓትነት መጠቀም ክልከላ ወይም ገደብ የለውም፡፡ ነገር ግን ማንኛውም ሰው ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል መረጃውን ከሚመለከተው አካልና ከባህሉ ባለቤቶች ፈቃድ ሳያገኝ ለንግድና ትርፍ፣ የግል ጥቅምን መሠረት

ላደረጉ ሌሎች ተግባራት ወይም ከባህሉ ጋር ተፃራሪ ለሆኑ ተግባራት መጠቀም የአገሪቱ ሕግ በሚደነግገው መሠረት ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

6.3.**ምዝገባው የተካሄደበት ቀንና ቦታ**(Date and place of data gathering)

ምዝገባውየተካሄደው ጥቅምት25 ቀን 2015 ዓ.ም. (November4, 2022) ነው፡፡ ይህን ኢንቬንቶሪ ለማከናወን መረጃ በዋናነት የተሰባሰበው ከኢትዮጵያ ሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር በተለይ ከሲቲ ዞን፣ከድሬዳዋ፣ጅግጅጋእንዲሁም ከጂቡቲና ከሶማሊያ ነው፡፡

6.4**ቅርሱንበአገርአቀፍደረጃየመዘገበውአካል** (Responsible body to the National Inventory /register of the element)

ቅርሱንበአገርአቀፍደረጃ የመዘገቡት በኢትዮጵያ ቅርስ ባለሥልጣን የቅርስ ጥናትና ምርምር ከፍተኛ ባለሙያዎች ገዛኸኝ ግርማ እና ቀለሟ መኮንን፣የሶማሌ ክልልየባህልና ቱሪዝም ቢሮ የባህል ባለሙያዎች እና ሲቲ ሄርቴጅ ፋውንዴሽን የተባለ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት መስራች አባላት እና ባለሙያዎች ማለትም ወይዘሮ አያን አሊ፣ አቶ አብዱራህማን ኡስማን እና አቶ አሊ አብዱላሂናቸው፡፡ ኢንቬንቶሪውን ያጸደቀው የባለሥልጣኑ የሥራ ክፍል /Approved by/ በኢትዮጵያ ቅርስጥበቃ ባለሥልጣን የቅርስ ኢንቬንቶሪ፣ ቁጥጥርና ደረጃ ማውጣት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

እንዱዓለም ግርማዩ
የቅርስ ጥናትና ምርምር
ዳይሬክቶሬት

መጋቢት 08 2015